ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org
ፕሮግራም፡ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 13 ሜትር ባንድ
Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on n25 meter band

## ዜና ዘገባ

**ጥር 3 ቀን 2006 ዓ.ም.**

### የወያኔ ባለስልጣኖች ለወያኔ ድርጅት ህልውና ሲባል በመካከላቸው ጊዜያዊ እርቅ ማድረጋቸ ታወቀ

በቢተው በላይ ሽምጋይነት በአዲስ አበባው እና በመቀሌው የህወሀት ቡድኖች መሀከል ተፈጥሮ የነበረው የከረረና የመረረ ጸብ ለግዜው በሚል ሰሞኑን በሽምግልና መጠናቀቁን ጉዳዩን ከሚያውቁ ወገኖች ማወቅ ተችሏል፡፡ በ1993 ዓ.ም በወያኔ መሪዎች ክፍፍል ወቅት የአፈንጋጩ ቡድን አባልና የደቡብ ክልል ሞግዚት የነበረው ቢተው በላይ የት እንዳለ ለብዙ ዓመታት ሳይታወቅ የቆየ ሲሆን በቅርቡ የወያኔ ድርጅትን ሕልውና ለማዳን ሲል ከተደበቀበት ወጥቶ አስታራቂ ሽማግሌ ሆኖ በመቅረብ ለግዜው ችግሩን ሊቀርፍ እንደቻለ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

መለስ ከሞተ በሁዋላ ነገሮች ሰፍተውና ጦዘው በወያኔ ቱባ ባለስልጣኖች መሀከል ልዩነቱ ከርሮ አንደኛው የሌላኛውን ቡድን በሙስና ሰበብ ወደ ዘብጥያ እየከተተ ውጥረቱ ግሎ እንደነበር የሚታወቅ ነው። በወያኔው ድርጅት ሊቀመንበርና በትግራይ ክልል ፕሬዝዳንት በአባይ ወልዱ የሚመራው የመቀሌው ቡድን ለጊዜው አሻፈረኝ ብሎ ለቀናት አስቸግሮ የነበረ ቢሆንም ከራሱ ቡድን ውስጥ እንደገና ሌላ ተቃውሞና ግፊት በመከሰቱ ምክንያት የእርቁን ጥያቄ ሳይወድ በግድ ሊቀበል እንደቻለም ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

በአባይ ወልዱ ሲመራ የነበረው የመቀሌው ቡድን እርስ በርስ ክፍፍል ከመፍጠሩም በተጨማሪ ኪሮስ ቢተው...ቴዎድሮስ ሐጎስ...ተክለወይኒ አሰፋ እና ሌሎቹም ባለስልጣናት ግጭት ውስጥ በመግባታቸው የተነሳ የቀድሞ አቋሞማቸው ሊቀጥል ባለመቻሉ እርቁን በተሸናፊነት ለመቀበል ተገድደዋል ሲል የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት የወያኔ ድርጅትን መዳከም የሚፈልጉ የራሳችን አጋር ድርጅቶች መኖራቸውን እያወቃችሁ ለ17 ዓመታት ደምተንና ቆስለን ብሎም ብዙ ወንድሞቻችንን ያስጨረስንበትን ትግል መና የሚያስቀር ሂደት ማድረግ ስለሌበችሁ በሰማዕታቱ አጽም ይገኙችሁዋለሁ በሰላም ጨርሱ እያለ መሬት ላይ እየተንከለባለለ ሲማጸናቸው የነበረው ቢተው በላይ ለወያኔ ህልውና ሲሉ ከልባቸውም ባይሆንም ከአንገት በላይ ባደረጉት እርቅ ተደስቶ ሲያነባ እንደነበር የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

ተደረገ በተባለው የእርቅ ሂደት ወቅት በሕወሀቱ ምክትል ሊቀመንበር በደብረጽዮን የሚመራው ቡድን የበላይነቱን እንዲይዝ የተደረገ ሲሆን የመቀሌው አባይ ወልዱ ቡድን ለግዜውም ቢሆን ሽንፈቱን አምኖ ይቅርታ እንዲጠይቅ ተደርጓል። በ 2007 ዓ.ም በሚደረገው ምርጫ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ስልጣን መልሰን መቆጣጠር አለብን በማለት ሁለቱም ቡድኖች አንድ አቋም መያዛቸው የታወቀ ሲሆን በተለይ በአሁኑ ሰዓት ከቴሌቪዥን እስክሪንና ከዓለም አቀፍ ስብሰባዎች የማይለየው የወያኔው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቴዎድሮስ አድሕኖም ቀጣዩ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆን አለበት በሚለው ሀሳብ ላይ በሁለቱም ወገን ስምምነት ላይ የተደረሰ መሆኑን ምንጮቹ ጠቅሰዋል።

በእርቁ ሂደት ላይ የእነ አባይ ወልዱ ቡድን ደጋፊና አባል የነበሩት እና በሙስና ለእስር የተዳረጉት የደህንነት ባለስልጣናት ከእስር እንዲፈቱ ጥያቄ ቀርቦ የነበረ ቢሆንም አጋር የ ብአዴኖችን..ኦህዴዶችን እና የደኢህዴኖችን አቋም ያጠናክራል በሚል የተጀመረው የፍርድ ሂደት እንዲቀጥል የሚል ስምምነት ላይ የተደረሰ መሆኑ ታውቋል።

በወያኔ ባለስልጣናት መሀከል ተደረገ የተባለው የእርቅ ሂደት ጊዜያዊ እንጂ ከልባቸው ተማምነውበት እንዳልሆነ የጠቀሱት ምንጮቹ በታሰሩት የወያኔ ባለስልጣናት ጉዳይ ቡድኖቹ ሰፊ ውዝግብ ውስጥ እንዳሉ ገልጸዋል፡፡

በተለይ ግዜ ጠብቀው አድብተው ስልጣን ከእጃችን ሊያወጡ ይችላሉ ብለው የሚሰጉትን ብአዴንና ኦህዴዶችን በልዩ ሁኔታ ክትትል የሚያደርጉባቸው ሲሆን በቅርቡም በአማራ ክልል ፕሬዝዳንት ላይ እና በሌሎችም ባለስልጣናት ላይ የተወሰደው ከስልጣን የማባረር እርምጃ ድርጅቶቹን ለማዳከም የተወሰደ እንደሆነ ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

የወያኔን ሕልውና አስጠብቆ ከመቀጠል ጋር በተያያዘ ብቻ እርቁ ወረደ ይባል እንጂ በውስጣቸው የተፈጠረው ክፍፍል እና ልዩነት መቼም ቢሆን መቼ በጸዳ እና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ይፈታል ማለት ዘበት አንዳንድን ውስጥ አዋቂ ወገኖች አስተያየት ይሰጣሉ።

## <u>የምስራቅ እዝ ዋና አዛዥ ተብየው ከኃላፊነቱ ተነሳ</u>

በወያኔ መከላከያ ጄኔራል ተብየዎች መሀከል የተጀመረው ሹም ሽረት ቀጥሎ ሰሞኑን ደግሞ የምስራቅ እዝ አዛዡ የወያኔው ሜ/ጄ/ል ተብየው ገ/እግዚአብሔር መብርሃቱ ተነስቶ የኦህዴዱ ሜ/ጄ/ል ጌታቸው የተሰኘው ግለሰብ መተካቱን ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለጹ፡፡

ባሳለፍነው ወር መጀመሪያ ላይ ጀምሮ ከፍተኛ የጦር አዛዦችን ከነበሩበት ቦታ እያነሱ በዝውውር ስም በየመምሪያው የሰዓት ፊርማ ብቻ እንዲፈርሙ ተደርገው እንዲቀመጡ መደረጉ ቀጥሎ ሰሞኑን የምስራቅ እዝ ዋና አዛዡ ተብየው መነሳቱ ታውቆዋል፡፡

ሳሞራ የኑስ ከሱ ጋር ንትርክ እና ውዝግብ ውስጥ ገባ በሚል የሰሜን እዙ ዋና አዛዥ ተብየውን ሳዓረ መኮንንን በዝውውር ስም ከስልጣኑ አንስቶ በዝቅተኛ መኮንን በሚመራው መምሪያ ውስጥ እንዲቀመጥ ባደረገ በጥቂት ቀናት ውስጥ የማዕከላዊ እዝ ዋና አዛዥ ተብየው የብአዴኑ አበባው ታደሰን ...እና የአየር ኃይል ዋና

አዛዥ ተበየውን የወያነውን ሞላ ኃይለማርያምን አንስቶ ያንሳፈፈ መሆኑ መሆኑ የሚታወስ ሲሆን ሰሞኑን ደግሞ የምስራቅ እዙን ዋና አዛዥ ማንሳቱ ታውቆዋል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በወያኔ ሲቪል ባለስልጣናት መሀከል የተፈጠረው ሽኩቻን ተከትሎ በመከላከያ ውስጥ ባሉ ጄኔራል ተብየዎችም በተለይ ከበረሀ በመጡትና በሚተዋወቁት መሀከል ቡጢ ቀረሽ ስድብ እየተለዋወጡ የተከፋፈሉ ሲሆን ሰሞኑን ነባር እና ትላልቅ ቦታዎች የያዙትን መኮንኖች እያንሳፈፉዋቸው መሆኑን ጉዳዩን ከሚከታተሉ ሰዎች ለማወቅ ተችሏል።

በዚህም መሰረት የሰሜን እዝ ..የማዕከላዊ እዝ..የምስራቅ እዝ ...የአየር ኃይል ዋና አዛዥ ተብየዎች የተንሳፈፉ ሲሆን በምትካቸውም ሌሎች የእዝ አዛዥነቱን ቦታ ተቆጣጥረውታል ሲሉ ምንጮቹ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

በምስራቅ እዝ አዛዡ በወያኔው ሜ/ጄ/ል ተብየው ሙብርሀቱ ገብረእግዚአብሄር ምትክ የኦህዴዱ ሜ/ጄ/ል ተብየው ጌታቸው የተባለው የተተካ ሲሆን በሰሜን እዝ አዛዥ ሌ/ጄ/ል ተብየው ሳዓረ መኮንን ምትክ የመከላከያ የትምህርትና ስልጠና ኃላፊ የነበረው ሜ/ጄ/ል ገብራት አየለ በማዕከላዊ ዕዝ ዋና አዛዥ ሌ/ጄ/ል ተብየው አበባው ታደሰም ምትክ ሌላ ለጊዜው ስሙ ያልታወቀና የሜ/ጄ/ል ማዕረግ ያለው መኮንን መሾሙ ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ሳሞራ የኑስ መከላከያን የራሱ ደጋፊ እና የቅርብ ወዳጅ የሆኑት ጄኔራል መኮንኖች እንዲቆጣጠሩት ለማድረግ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ያስረከባቸው ሲሆን በሚቀጥለው ዓመት የመከላከያ ኤታማዦር ሹምነቱን ስልጣን በሚለቅበት ወቅት በቅርቡ በወያኔ የሌ/ጄ/ል ማዕረግ የተሰጠው ዮሀንስ ገ/መስቀል እንዲረከበው ውስጥ ውስጡን እየሰራ መሆኑን ምንጮቹ ገልጸዋል፡፡

የመከላከያ ደህንነት ተቋዋም የሆነውን መምሪያ የወያኔው ብ/ጄ/ል ተብየው ተክለብርሀን አረጋዊ እንዲቆጣጠረው ያደረገ በወያኔ የብ/ጄ/ል ማዕረግ የተሰጣቸው ህንጻ ወ/ጊዮርጊስ፤ ገብሩ ገብረመስቀል፤እና መአሾ በቀጣይነት መከላከያን የሚቆጣጠሩ የወያኔ መኮንኖች መሆናቸው ታውቋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት በመከላከያ ውስጥ ሰራዊቱ የተለያዩ ጥያቄዎችን ለማዳፈን አንዱን ክፍል ከሌላው ጋር እያሰባጠሩት ሲሆን ለአጭር ኮርስ እየተባለም የበታች ሹሞችን በተለያዩ የወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ አስገብተው የፖለቲካ ትምህርት እየሰጡ ማስመረቃቸው ታውቆዋል፡፡

ሰሞኑንም የሰሜን እዝ የበታች ሹም ማሰልጠኛ ማዕከል አዛዥ የሆነው በርሔ ወ/ጊዮርጊስ ማሰልጠኛ ካምፕ በሺህዎች የሚቆጠሩ የበታች ሹሞችን አሰልጥኖ ማስመረቁ ከዚሁ የጦሩን ውጥረት ከማርገብ ጋር የተያያዘ መሆኑንም ምንጮቹ ጠቁመዋል፡፡

## የመላኩ ፈንታ ጉዳይ የፌዴራሽን ምክር ቤት አባሎችን ለሁለት ከፍሎ ሲያፋልም መሰነበቱ ታወቀ

በወያኔ ባለስልጣናት መሀከል በተፈጠረ ልዩነት እና ሽኩቻ ምክንያት በሙስና ዘብጥያ የወረደው የመላኩ ፈንታ አቤቱታ በምክር ቤት አባሎች ጭምር ሲያወዛግብና ሲያጨቃጭቅ መሰንበቱ ታወቀ፡፡

በሚኒስትር ማዕረግ የገቢዎች እና ጎምሩክ ባለስልጣን ዳይሬክተር የነበረውና በሙስና ሰበብ ለእስር የተዳረገው መላኩ ፈንታ ባለኝ መብት እና በሕጉ መሰረት በከፍተኛ ፍርድ ቤት ሳይሆን በጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ሊታይልኝ ይገባል በሚል ባቀረበው አቤቱታ ዙሪያ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባሎችን ለሁለት ከፍሎ ሲያፋትጋቸው መሰንበቱ ታወቀ፡፡

የብአዴን ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የነበረው መላኩ ፈንታ በሙስና ተብሎ ለእስር ከተዳረገ በሁዋላ ጉዳዩ በከፍተኛው ፍርድ ቤት መታየት ቢጀምርም የእኔ ጉዳይ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ብቻ ነው ሊዳኝ የሚገባው ብሎ ባቀረበው ማመልከቻ መሰረት የፌዴሬሽን ምክር ቤት በጠራው አስቸኳዋይ ስብሰባ ላይ በአባሎቹ መሀከል መስማማት ጠፍቶ እርስ በርስ ሲያነታርካቸው እንደነበር ታውቆዋል፡፡

በብአዴኑ ከሳ ተክለብርሀን አፈ ጉባኤነት የሚመራው የፌዴሬሽን ምክር ቤት በጠራው በዚሁ አስቸኩዋይ ስብሰባ ላይ ሀሳቡ ቀርቦ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታይለት አይታይለት በሚለው አጀንዳ ዙሪያ ዱላ ቀረሽ ሙግት ገጥመው የነበረ ሲሆን በተለይ ከአማራ ክልል የመጡ የምክር ቤቱ አባሎች ግለሰቡ ሕገ መንግስቱ የሰጠውን መብት ተጠቅሞ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊታይለት እንደሚገባና ከዚህ ቀደምም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የብአዴን ሊቀመንበር የነበረው ታምራት ላይኔ በጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደታየለት ገልጸዋል፡፡

አክለውም ዛሬ በእስር ላይ የሚገኘው መላኩ ፈንታ በተጠረጠረበት የሙስና ክስ በሕገ መንግስቱ ላይ ቁልጭ ብሎ ሰፈሮለት የሚገኘውን መብቱን ወደ ጎን በማድረግ በጥቂት ግለሰቦች ፍላጎት ብቻ አይታይለትም ብለን የምንወስን ከሆነ ወትሮም ስንጠራጠር የነበረውን የታሰረበትን ምክንያት አጉልቶ የሚያወጣ ነው በማለት ከአማራ ክልል የመጣ ካድሬ ተናግሮዋል፡፡

የመላኩ ፈንታ ጉዳይ በጠቅላይ ፍርድ ቤት አይታይም ብላችሁ የምትወስኑ ከሆነ ከዚህ ቀደም የብአዴን ሊቀመንበር የነበረው ታምራት ላይኔ የታየበትም ሂደት ተገቢ ያልሆነና ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን በይፋ ለሕዝብ በግልጽ ልትነግሩ ይገባችሁዋል ያለው ይሄው የምክር ቤት አባል ካድሬ በጠቅላይ ፍርድ ቤት እንዲታይለት በሙሉ ድምጽ ልንወስንለት ይገባል ሲል አጽንኦት ሰጥቶ ተናግሮዋል፡፡

ሌላው የምክር ቤት አባል ደግሞ ከዚህ ቀደም የታምራት ላይኔ ጉዳይ በጠቅላይ ፍርድ ቤት የታየለት መሆኑን አምኖ ነገር ግን ግለሰቡ በወቅቱ ጥያቄ ባለማንሳቱ በነበረበት እንዲቀጥል ሲደረግ አሁን ግን ወደ ሁዋላ መለስ ብለን ስንመለከተው ህጉ ስህተት እንዳለበት ነው በሚል አሳማኝ ያልሆነ መከራከሪያ ያቀረበ ሲሆን በሁለቱ ቡድን መሀከል ሙግት የተደረገ ቢሆንም በድምፅ ብልጫ በሚል በከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲታይ የሚለው ውሳኔ ማግኘቱ ታውቆዋል፡፡

በባህር ዳር ከተማ 9ኛ መደበኛ የወያኔ ጠቅላላ ጉባኤ በተካሄደበት ወቅት የወያኔ ሰዎች አላሰራ ብለው አስቸግረውኛል በማለት በይፋ በመግለፁ የተበሳጩት የወያኔ ባለስልጣናት መላኩ በመድረክ ላይ በተናገረ አንድ ወር ግዜ ውስጥ የሙስና ክስ አዘጋጅተው ለእስር የዳረጉት መሆኑን በወቅቱ በስፋት መዘገባችን አይዘነጋም፡፡